ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ቡድን በሜልበርን

Democracy for Ethiopia Support Group In Melbourne

# 2014

# ከወያኔ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሾልኮ የወጣ




## ዲያስፖራውን የመሰለያ እቅድ

ለአረመኔ መንግስት የሚሰልል አረመኔ ነው!

ከዚህ በታች ከገጽ 6 እስከ 13 የተቀመጠው የወያኔ የስለላ እቅድ ሰነድ ከሁለት አመት በፊት ማለትም በ 2004 የተነደፈና አሁን በስራ ላይ የዋለ ነው።

ይሁን እንጂ ወያኔ ዲያስፖራውን የመሰለል እቅድ ነድፎ መንቀሳቀስ የጀመረው ከፉኛ ሽንፈት/ውርደት በገጠመው በምርጫ 1997 ማግስት መሆኑን የሚያረጋግጠው፡ በ1998 የወጣው ባለ 52 ገጽ የስለላ እቅዱ በገጽ 5 ላይ የሚገኘውን ሊንክ በመጫን ማንበብ ይችላሉ።

**አንብበው ላላነበበ በማስተላለፍ**

**የዜግነት ግዴታዎን ይወጡ!**

# አጭር መግለጫ በመላው ዓለም ለምትገኙ ፤

**የሀገራችሁ መጻኢ ህልውና፤ የወገናችሁ የዘመናት ጭንቅ፤ እንግልትና ፤ የስቃይ ህይወት ሌት ተቀን ለሚያሳስባችሁ ውድ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ፡-**

ከሁለት ዓመት በፊት የወያኔ መንግስት በውጭው ዓለም የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ ለመሰለል የነደፈውን እቅድ በዝርዝር የሚገልጽ ሚስጥራዊ ሰነድ ከውጭ ጉዳይ መስራቤቱ ሾልኮ ወጥቶ በመላው ዓለም ለሚገኘው ኢትዮጵያዊ በተለያዩ ድህረ ገጾች ይፋ መሆኑ የሚታወስ ነው። ሾልኮ የወጣው ሰነድ ባጋጣሚ በእንግሊዝ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን ለመሰለል የተነደፈን እቅድ የሚዘረዝር ይሁን እንጂ እቅዱ በመላው ዓለም በሚገኘው የመንግስት ተቃዋሚ ላይ ሁሉ ተግባራዊ እንዲሆን ታስቦ የተቀመረ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው።

በመሆኑም በየትኛውም ሃገር የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ይህንኑ ዝርዝር የስለላ እቅድ ተገንዝቦ ቅድመ ዝግጅት ያደርግ ዘንድ ከሁለት ዓመት በፊት በየድህረ ገጹ እንዲበተን ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ ይህን የሚስጥር ሰነድ ምን ያህሉ ኢትዮጵያዊ ወገን አግኝቶት አንብቦታል? ምን ያህሉስ ተገንዝቦታል? ምንስ አይነት ጥንቃቄ አድርጎ ቆይቷል? የሚሉትን ጥያቄዎች ስናነሳ የምናገኘው ምላሽ ብዙም የሚያመረቃ አይመስለንም።

ይህን የምንለው ያለ ምክንያት አይደለም። በአካባቢያችን ከምናየው እውነታ በመነሳት እንጂ!። አዎ ኢትዮጵያዊው ወገን ይህ ከሁለት ዓመት በፊት ሾልኮ የወጣው ሰነድ በእቅድ ደረጃ የያዛቸውን ንድፈ ሃሳቦች አንብቦ ፤ተገንዝቦና ብሎም ትኩረት ሰጥቶ ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ አላደረገም። ይህን ባለማድረጋችንም እንሆ የወያኔ መንግስት የሁለት ዓመቱን የመረጃ ስብሰባ(ስለላ) እቅድ ያለምንም እንከን አጠናቆ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገብቷል።

ለአንባቢያን ሙሉ ግንዛቤ ይሰጥ ዘንድ ከወያኔ የውጭ ጉዳይ መስሪያቤት ሾልኮ የወጣውን የስለላ እቅድ ኮፒ ከዚህ ማብራሪያ ጋር አባሪ አድርገን አቅርበነዋልና አንብበው ሙሉ ይዘቱን ይመረምሩ ዘንድ እምነታችን ነው።

ይህ በእንዲህ እያለ፡- ይህ ማብራሪያ ከተዘጋጀበት ከሜልበርንና በተጓዳኝም ከአውስትራሊያ የተለያዩ ስቴቶች ወቅታዊ እንቅስቃሴ በመነሳት የወያኔ መንግስት የመረጃ ስብሰባውን(ስለላውን) አጠናቆ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ አስረጂ ይሆናሉ ያልናቸውን ነጥቦች ማመላከት እንሻለን።

ትኩረታችንን ከሳቡትና በዚህ ማብራሪያ ልናካትታቸው በመረጥናቸው ንዑስ ርዕሶች ሥር የሚገኙ በወያኔ መንግስት የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆች ላይ በማተኮር እንደሚከተለው፤ የወፍ በረር ምልከታ እናደርጋለን።

## በታዋቂና በተሰሚ ሰዎች ስለመጠቀም፤ ተቃዋሚና ደጋፊን ስለመለየትና ስለ ደጋፊዎች አደረጃጀት ለሚሰበሰቡ መረጃዎች የቀረቡ መጠይቆች፡-

- ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች ተለይተዋል? ከተለዩስ እነማን ናቸው? እነሱን ለመጠቀም ምን ተሰርቷል? ለወደፊቱስ ምን መስራት ይቻላል? ተሰሚነት ያላቸው የኪነት ሰዎች አሉ? እንዴት እንጠቀምባቸዋለን? በሚዲያስ በኩል ለምሳሌም በጽሁፍ፤ በሬዲዮ፤ በጋዜጣ፤ በኢንተርኔት፤የሚሰሩ ደጋፊዎቻችን እነማን ናቸው የሚቃወሙትስ እነማን ናቸው? አንድ ለአምስት የሚባለው አደረጃጀት ተጀምሯል? እንዴት ይካሄዳል?

## ዲያስፖራው የሚገኝባቸውን ልዩ ልዩ ተቋማትና የንግድ ቤቶችን፤ እድሮችን፤ ልዩ ልዩ ሕዝባዊ መድረኮችን ለመሰል የወጡ መጠይቆች

- ዲያስፖራው የሚገኝበት የባህል ምግብ ቤት፤ ሱቅ፤ የሃይማኖት ተቋማት፤ ልዩ ልዩ መድረኮች ይታወቃሉ? እነ|ኘህን ለመጠቀም ምን የተደረገ ነገር አለ? ከሌለ ለወደፊቱ እንዴት ይቻላል?ሌሎች ስለ ዲያስፖራው መጠቀስ ያለባቸው ነገሮች ካሉ....።

## በዲያስፖራ የተወለደውን ወጣቱን ትውልድ ለማጥመድ የወጡ መጠይቆች

- ወጣቱን ትውልድ በተመለከተ አደረጃጀት ካለ? የወጣቱ ዝንባሌ ? ከኛ ጋር የመስራት ፍላጎት እንዲኖረው እንዴት ማድረግ ይቻላል? ከዚህ ጋር በተያያዘ የተሰሩ ስራዎች ካሉ።

## የዲያስፖራውን ገንዘብ አላላክና አካውንት ስለመክፈት መረጃ ለመሰብሰብ የወጡ ጥቄዎች

- የዲያስፖራው የገንዘብ አላላክ ምን ይመስላል? የሃገራችን ባንኮች አሰራር? ህጋዊ መልክና ህጋዊ ባልሆነ መልክ እንዴት ይለካል? በሃገራችን ባንኮች አካውንት የከፈተ አለ?

## ተቃዋሚ ድርጅቶችን ለመሰለል የወጡ ጥያቄዎች በተመለከተ

- ዋና ዋና ተቃዋሚ ድርጅቶች ማን ማን ይባላሉ? ዋና ዋና አመራሩ ማን ይባላሉ? የሚንቀሳቀሱበት ሃሳብ ምንድነው? የአባላቱ ብዛት? ያላቸው ድጋፍ? በአባላቸው ሳይቀር የሚነሱ ተቃውሞዎች ምንድናቸው? የሃገሩን መንግስት ኢንፉለንስ በማድረግ ደረጃ ያላቸው ሚና? ሰዎችን ለማግኘት፤ የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ምንድናቸው? አሰራራቸው ምን ይመስላል። በተቃውሞ በዋናነት የሚንቀሳቀሱ ሰዎች እነማን ናቸው?

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆች ለምልከታችን ግብአት ይሆናሉ ያልናቸው በሰነዱ ከተካተቱት ጥቂቶቹ ናቸው። እንግዲህ በመነሻችን ላይ እንደጠቀስነው የወያኔ መንግስት በነኚህና በሌሎቹም ጥያቄዎች መሰረት ከዲያስፖራው መረጃ የመሰብሰቡን እቅድ የነደፈው ከሁለት አመት በፊት ነው፡

## ባለፉት ሁለት አመታት ምን ሠሩ?

- ባለፉት ሁለት ዓመታት አፍቃሪ-ወያኔዎች ከሁለት አመት በፊት በወጣው የስለላ መጠይቅ ላይ በመመርኮዝ መረጃዎቹን ሲሰበስቡ ቆይተዋል። በዚሁ መሰረትም፤ ታዋቂ ሰዎች፤ ተሰሚ ሰዎች፤ የኪነት ሰዎች፤ ጠንካራ ተቃዋሚዎች ፤ ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች፤ ተቃዋሚ ሚዲያዎች፤ ደጋፊ ሚዲያዎች፤ ተለይተዋል።ዲያስፖራው የሚንቀሳቅስበትን ተቋማት ጠንካራና ደከማ ጎን አጥንተዋል። ጠንካራውን ተቃዋሚ ሊደለል ከሚችለው ተቃዋሚ ለይተዋል፡፤

## አሁን ምን እየተተገበረ ነው? :-

- በአሁን ሰዓት ደግሞ ለሁለት አመታት ሰስብስበው በላኩት መረጃ ላይ ተመስርቶ የተላከላቸውን መመሪያ በመከተል ወደ ተግባር እንቅስቃሴ ገብተዋል፡፤ ታዋቂ ሰዎችን ፤ የኪነት ሰዎችን ፤ አግባብቶ መጠቀም፤ የሚዲያ ሰዎችን ማጥመድ፤ መመልመል፤ ብሎም አንድ ለአምስት ማደራጀት ይዘዋል።
- ደጋፊ ሚዲያዎቻቸውን በፕሮፓጋንዳ አስታጥቀው እያንቀሳቀሱ ይገኛሉ። ደጋፊዎቻቸውን በተለያዩ ተቋማት ለምሳሌ በሃይማኖት ተቋማት፤ በኮሚኒቲ፤ በስፖርት እንቅስቃሴ፤ በውይይት መድረክና በሌሎችም ሲቪክ ማህበራት ፤ በአመራርነት አስርገው በማስገባት ቢቻል ተቋሙን ለመቆጣጣር ካልተቻለም ተቋማቱ ጸረ ወያኔ እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ ለማዳከም እየሰሩ ይገኛሉ፡፤
- በእቅዳቸው አዲሱ ትውልድ ብለው የጠሩትን በውጭው ዓለም የተወለዱ አልያም በህጻንነት መጥተው ዛሬ በወጣት እድሜ ክልል የሚገኙትን ልጆቻችንን በተለያየ ጥቅማጥቅም አማለው በደጋፊነት እየመለመሉ ይገኛሉ።
- በ40/60 የኮንደሚንየም ቤት ምዝገባ ደጋፊዎችን ለማበራከት በትጋት እየሰሩ ይገኛሉ፡፤ በተለያዩ ሽቀጦች አስመጭና ላኪነት በአነስተኛ ወይም ነጻ ቀረጥ እንዲሰሩ በማባበል ደጋፊዎችን እየመለመሉ ይገኛሉ፡፤
- በተለያየ ጥቅማ ጥቅም ተደልለውም ሆነ በሌላ ምክንያት በደጋፊነት የተመለመሉ አባላትን 1 ለ 5 (4 አባል አንድ ሃላፊ) አድርገው በማደራጀት ዲያስፖራውን እንዲሰልሉ፤ ብሎም በየግዜው ከመንግስት የሚወርድን መመሪያ እንዲተገብሩ አሰማርተዋል፡፤ በ 1 ለ 5 የተደራጀው ሴል በየግዜው እየተገናኘ ስራውን ይገመግማል ኢንፎርሜሽን ይለዋወጣል፤ በግምገማውም ጠንካራው ተወድሶ ፤ ደካማው ተወቅሶ፤ ለነገ ደግሞ አዲስ መመሪያ ይቀበላል።
- የተመለመሉት ደጋፊዎች ከስለላውና ተቃዋሚን ከማዳከሙ ተልዕኮ በተጨማሪ የአባይን ቦንድ መሸጥ፤ የአምስት አመቱን የትራንስፎርሜሽን እቅድ መስበክ ፤ የወያኔን ልማታዊ መንግስትነት በዲያስፖራው ውስጥ ለማስረጽ መስራት ይጠበቅባቸዋል። ደጋፊ ሚዲያዎች በተለይ የመንግስትን መልካም ስም በመገንባት ረገድ ብዙ ይጠበቅባቸዋል። ከዚሁ በተጓዳኝ በተቃዋሚው ወገን በመንግስት ላይ የሚቀርቡ ክሶችን በማስተባበል ይሰራሉ።

## በወያኔ መንግስት ደጋፊዎች እየተተገበሩ ናቸው ላልናቸው ስራዎች አካባቢያዊ መገለጫዎች

ይህ ማብራሪያ የተዘጋጀው በሜልበርን ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ቡድን በመሆኑ አካባቢያዊ መገለጫዎቹም ከሜልበርን ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ እንቅስቃሴ የተመዘዙ ሊሆኑ ግድ ነው። ይሁንና የወያኔ መንግስት የስለላ እቅድና አካሄድ ተመሳሳይ በመሆኑ በየትኛውም አገር የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ከዚሁ ሰነድ በመነሳት የራሱን አካባቢያዊ መገለጫዎች ሊያመላክት ይቻለዋል።

- በተለይ በሜልበርን፤ በተለያየ ግዜ ኮሚኒቲውን ለማዳከም፤ የስፖርት እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር፤ ቤተ ክርስቲያናቱን ለመለያየት የተደረጉ ነገር ግን ያልተሳኩ ሙከራዎች ተቋማትን የመቆጣጠር እንቅስቃሴያቸው መገለጫ ናቸው፡፤
- በቅርቡ ከሜልበርን አስር የሚሆኑ ወጣቶች ተመልምለው ለስልጠናና ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ መሄዳቸው ወጣቱን ትውልድ የመቆጣጠር እቅድ መገለጫ ነው።
- ከዚህ በፊት በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ማህበራዊ ግልጋሎት እንዲሰጡ ሲመረጡ፤ ልዩ ልዩና ሰንካላ ምክንያቶች እየደረደሩ ይሸሹ የነበሩ በርካታ ግለሰቦች፤ ዛሬ መድረክ አይቅረን ብለው በየቦታው ሲጣዱ የማየታችን ሚስጥርም በተቋማት ሰርጎ የመግባቱ ትልም መገለጫ ነው።
- ከወያኔ ኤንባሲ ጋር በቅርበት በመስራት የተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ለማስፋፋት የሚሰራ የንግድ ድርጅት በይፋ እራሱን ማስተዋወቁም ሌላው መገለጫ ነው፡
- አዲሱ አምባሳደር በተለያዩ የአውስትራሊያ ስቴቶች በመዟዟር ይህን ለሁለት ዓመታት መረጃ የተሰበሰበበትን ተልዕኮ ለማስፈጸም እንቅስቃሴ መጀመራቸውም ዋናውና ወቅታዊው መገለጫ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ አንባቢያን ከዚህ መግለጫ ጋር የተያያዘውን የስለላ እቅድ ሰነድ በማንበብ ሌሎችም በርካታ መገለጫዎች ሊያመላክቱ እንደሚችሉ እርግጥ ነው።

## የአዲሱ አምባሳደር ተልእኮ

አዲሱ አምባሳደር በተለያዩ የአውስትራሊያ ስቴቶች በመዟዟር ይህን ለሁለት ዓመታት መረጃ የተሰበሰበበትን ተልዕኮ ለማስፈጸም እንቅስቃሴ መጀመራቸውም ታውቋል። አምባሳደሩ ኢትዮጵያዊያንን ሰብስበው ለማነጋገር እቅድ እንዳላቸው ተሰምቷል።

ይህን እቅድ ለማሳካት የተነደፈው ዘዴ ደግሞ ደጋፊዎቻቸው ተቃዋሚ በመምሰል አምባሳደሩ በጠራው ስብሰባ ላይ ተገኝተን **ልክ ልኩን** እንንገረው በሚል እውነተኛና የዋሁን ተቃዋሚ ማሳሳት ነው። ተቃዋሚው **ልክ ልኩን** ልንገር ብሎ በስብሰባው ሲታደም፦ የአባይ ግድብና ፤ የ5 ዓመቱ የትራንስፎርሜሽን ዲስኩር ቀዳሚ አጀንዳዎች እንደሆኑ ይነገረዋል። ጥያቄ ካለ መጨረሻ ማቅረብ ይቻላል ይባላል። በሁለቱ አጀንዳዎች ውይይት ሲደረግ **"የዲያስፖራ ኢትዮጵያዊያን መንግስት የሚያደርገውን የልማት እንቅስቃሴ አደነቁ"** ለሚለው የኢቲቪ ድራማ ግብዓት የሚሆን ቪዲዮ ይቀረጻል። ወደ ጥያቄው ክፍለ ግዜ ሲገባም ልማታዊ ጥያቄዎች ካልሆኑ አይስተናገዱም በሚል መድረኩ ይዘጋል።
በመሆኑም ስብሰባው ቀዳሚ አጀንዳው የሰብዐዊ መብት አጠባበቅ፣ የጸረ ሽብር ህጉ፣ የፕሬስ አፈናው፣ የዜጎች መፈናቀል፣ የፖለቲካ ምህዳሩ መጥበብ እና መሰል አንገብጋቢ ችግሮቻችን እንዳለመሆናቸው በተመረጡ የመሸንገያ አጀንዳዎቻቸው ዙሪያ ላለሙት የፖለቲካ ግብ እንዳያውሉት ልናስቆማቸው ይገባል።

ይህ እቅዳቸው በአንዳንድ ቦታዎች ተሞክሮ ብዙም እንዳልተሳካላቸው ተረድተናል።እኛም ከዚህ ተምረን ልክ ልካቸውን እንገራቸው የሚሉንን ልክ ልካቸውን ልንነግራቸው ይገባል፡፤ መጀመሪያ የሰሚ ያለህ፤ የፍትህ ያለህ፤ የሚለውን የሃገርቤቱን ወገን አነጋግሩ፣ አድምጡ፣ ልንላቸው ይገባል!። ስብሰባው እንዳይካሄድም የምንችለውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅብናል።

## የወያኔ ደጋፊዎች ከመንግስት የሚያገኙት መደለያና ጥቅማ ጥቅም ምንድነው?

የወያኔ መንግስት ደጋፊዎቹን የሚደልልበት የጥቅማ፡ጥቅም አይነቶች የተለያዩ ናቸው። በዋናነት ግን የግለሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ መረጃዎች አሉ። ለምሳሌ የንግድ ቦታ ለሚፈልግ የንግድ ቦታ ፤ ቤት መስሪያ ቦታ ለሚፈልግ እንዲሁ፤ ኮንደሚንየም ለመግዛት ለሚሻ ኮንደሚኒየም ፤ ለመነገድ ለሚሻ አነስተኛ ወይም ከቀረጥ ነጻ ንግድ ፤ ሌሎችም ይፈቀድለታል/ይደረግለታል። ...ከዚህ በተጨማሪ በሃገርቤት አወዛጋቢ የውርስና የይገባኛል ጉዳይ ያላቸው ጉዳያቸውን ለማስፈጸም ሲሉ በደጋፊነት እንደሚመለመሉም፣ ተደርሶበታል።

## ዲያስፖራው ምን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል?

- ከሁሉ አስቀድመን ከዚህ መግለጫ ጋር የተያያዛውን የስለላ እቅድ በጥሞና አንብበን ላላነበበም አስነብበን ልንወያይበትና ልናብላላው ይገባል። በደንብ ከተረዳነው አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ እንችላለን።
- የወያኔ ጥንካሬ ሁሉ በኛ ልዩነትና አለመግባባት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ አሁንም ከሁሉ አስቀደመን መነጋገር ፤ ሃሳብ መለዋወጥ፤ ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት መፍቀድን እንደ መርህ መቀበል ይገባናል።ግላዊና ጥቃቅን ልዩነቶችን አስወግደን ትኩረታችንን ሁሉ በአንዱና በዋናው ጠላት በወያኔ ላይ ማድረግ።
- በኮሚኒቲ፤ በቤተክርስቲያን[ በስፖርትና በሌሎችም ተቋማት ውስጥ ቅራኔ የሚያጭሩ ሃሳቦችን መመርመር ምንጭና ምክንያታቸውን ማጤን።አፈንጋጮችን መከታተል።

- የህዝብን ሰባዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ለማስጠበቅና የሃገራችን ህልውና መታደግ የዜግነት ግዴታ እንጂ ፖለቲከኛ የመሆን ያለመሆን ምርጫ አለመሆኑን ተረድተን ፖለቲካ አያገባኝም የሚልን አዳካሚና አደንዛዥ አመለካከት መዋጋት።
- አሉባልተኞችን ማጋለጥ፤ የተለየና አስጊ እንቅስቃሴ ሲታይ መመርመር።ያለ ይሉኝታም ማጋለጥ።
- ወጣቶች እንዳይታለሉ መምከር፤
- የመንግስት ደጋፊነታቸው የሚታወቁ ሰዎችን አካሄድ መመርመር ለማያውቃቸው ማሳወቅ፤ የሚፈልጉትን መረጃ እንዳያገኙ ማግለል።ንግድ ቤት ካላቸውም በንግድ ቤታቸው አለመጠቀም። በሃዋላ ገንዘብ በመላክ የሚሰሩም ካሉ በነሱ በኩል ገንዘብ አለመላክ።
- በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የወያኔን መንግስት ኢሰብአዊና አረመኔያዊ ተግባር ማጋለጥ
- የተለያዩ ተቃዋሚ ድርጅት አባላት ልዩነታቸውን ወደ ጎን አድርገው ከላይ በተዘረዘሩት የጥንቃቄ እንቅስቃሴዎች እጅና ጓንት ሆነው መስራት ይገባቸል።
- ከሁሉም በላይ ደግሞ መቻቻል መቻቻል መቻቻል! ይገባናል እንላለን።

## ማጠቃለያ፡

ከሁለት አመት በፊት ሾልኮ የወጣውን ከዚህ በታች የምታነቡትን የስለላ እቅድ ሰነድ በግዜው በቂ ትኩረት ሰጥተነው ቢሆን ኖሮ ዛሬ በዚህ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ባልተገኘን ነበር። አሁንም ቢሆን ተቀራርበን፤ ተቻችለንና ተግተን ከታገልን ከድሃው ህዝብ ላብና ደም መጠው፤ ለከርስ አደሮች በሚከፍሉት መሸሩፍ የሰበሰቡት መረጃ ከወረቀት አልፎ የሚፈይደው ነገር አይኖርም። እንተባበር፤ እንነጋገር እንቻቻል! አንከፋፈል!


## ማስታወሻ

ከዚህ በታች በ 6 እስከ 14 የተቀመጠው የወያኔ የስለላ እቅድ ሰነድ ከሁለት አመት በፊት ማለትም በ 2004 የተነደፈና አሁን በስራ ላይ የዋለ ነው።

ይሁን እንጂ ወያኔ ይህን የስለላ እቅድ ነድፎ መንቀሳቀስ የጀመረው በምርጫ 1997 ከፉኛ ሽንፈት በገጠመው ማግስት መሆኑን የሚያረጋግጠው በ1998 የወጣው ባለ 52 ገጽ የስለላ እቅዱ ነው። ሰነዱን እዚህ ላይ ተጭነው ያንብቡ አንብበውም ያስነብቡ!!!

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ቡድን በሜልበርን



መግቢያ

በውጭ ጉዳይ ስራችን ዲያስፖራው ሀገራዊ መግባባት ፈጥሮ ራሱንና አገሩን የሚጠቅም ስራ በመስራት ሀገራችንን ከድህነት ለመውጣት በምታደርገው ጉዞ የራሱን ሚና እንዲጫወት ማድረግ አንዱና ዋና ስራዎቻችን እንዱ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም በሚሲዮኑ በኩል ስራዎች መስራታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ስራውን ለመቀጠል ለስራ መነሻ የሚሆን ነገር ለማግኘት ይህ የጥናት እቅድ (ToR) ተዘጋጅቷል። ጥናቱ በመጪው ዓመት ለሚካሄደው እቅድ መነሻ እንደሚሆንም ይጠበቃል።

1. የጥናቱ ዓላማ

   የጥናቱ ዓላማ የትግራይ ዲያስፖራ ያለው ሁኔታ በመዳሰስ ለቀጣይ ዓመት ለሚዘጋጀው እቅድ ግብአት ማድረግ።

2. የጥናቱ ወሰን በሚገኙት የትግራይ ዲያስፖራን የሚመለከት ሆኖ የሌሎችን አጠቃላይ በሆነ መንገድ የሚዳስስ ይሆናል።

3. የጥናቱ አቀራረብ

   - በመጀመሪያ አሰባሁን በአደረጃጀት ወስጥ ያሉትን በማሳተፍና ያሉትን ሰነዶች በመዳሰስ ይታያል። ከዚህ ውጭ ገለልተኛ የሆኑ ወይ ተሳትፎ የሌላቸውን በስልክ በማነጋገር የተሟላ እንዲሆን ማድረግ።
   - ጥናቱ ከስራ ጋር ባለው ወቀሚታ ትኩረት በማድረግ በመጨረሻም ተቋማዊ በሆነ መንገድ አስተያየት ተሰጥቶበት እንዲቀጥ ማድረግ።

## የትግራይ ተወላጆች ዲያስፖራ ስራ ለመጀመር አጠቃላይ ጥናት

1. ዓላማ
2. የጥናቱ ወሰን
3. የጥናቱ አቅጣጫ
4. የጥናቱ ዋና ዋና ትኩረት
   - 4.1 ስለ ሀገሪቱ (UK) አጠቃላይ ሁኔታ
   - 4.2 ስለ ዲያስፖራው አጠቃላይ ሁኔታ
     - 4.2.1 የኢትዮጵያ በአጠቃላይ እና የትግራይ ተወላጆች ዲያስፖራ እንዴት እንደመጡ፣ ብዛቱ፣ የብሄረሰብ ስብጥሩ ወዘተ
     - 4.2.2 በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበረው ሁኔታ
     - 4.2.3 ዲያስፖራው በዚህ አገር (UK) የሚደርስበት ችግር በሚመለከት ያለው ሁኔታ
     - 4.2.4 በሀገራችን ስለሚደረገው እንቅስቃሴና ስለሚሰጠው ግልጋሎት፣ የሚያነሳው ችግር
     - 4.2.5 በዲያስፖራ ስም የተደራጁ የተለያዩ አካላትን በሚመለከት
     - 4.2.6 ዲያስፖራው ከአገሩ ባህል ጋር እንዲቀሳሰር በማድረግና በተለይም የወጣቱ ሁኔታ
     - 4.2.7 ዲያስፖራ ከአገራችን በቢዝነስ በኩል ያለው ትስስር
     - 4.2.8 ዲያስፖራውና remitance እና የአካውንት መከፈት
     - 4.2.9 የዲያስፖራውና የቦንድ ሽያጭ
     - 4.2.10 የብሔራዊ መግባባትና የአንድ ለአምስት ያለው አደረጃጀት ሁኔታ
     - 4.2.11 ዲያስፖራና communication ሁኔታ
     - 4.2.12 ሌሎች መጠቀስ ያለባቸው ጉዳዮች
   - 4.3 ስለ የኢህአዴግ ድርጅቶችና አባላት በሚመለከት
   - 4.4 የተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚመለከት
   - 4.5 የኤርትራ ዲያስፖራ ሁኔታ
   - 4.6 የኢምባሲው የውስጥ አሰራርና የስራ ግንኙነት (ከዲያስፖራው ጋር በተያያዘ)
5. የጥናቱ ማጠቃለያ
   - ከተሰጠ የቃለ መጠይቅና፣ የሰነድ መረጃው ይሰበሰባል፣
   - በተያዘው መሰረት ዋና ዋና ጉዳይ ላይ ይጨመቃል፣
   - መሰረታዊ ድርጅት፣ ሌላ የሚመለከተው አካል ካለውና አስተያየት ከሰጠበት በኋላ ለስራ መነሻ ይሆናል።
   - የጥናቱ ዋና ዋና Recommendation ይቀመጣል።

| ተ.ቁ. | የጥናቱ ይዘት | አግባብ ያላቸው የሚጠየቁ ሰዎች | የግዜ ሰሌዳ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|
| 4.1 | ስለ UK አጠቃላይ ሁኔታ<br>• የህዝቡ ታሪካዊ አመጣጥና ከሰራችን ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ባህሉች፣ ዋና ዋና ከተሞች<br>• የሕዝቡ ብዛት<br>• የኢኮኖሚ መሰረት (export, import)<br>• Unemployment<br>• Inflation<br>• በህዝቡ የሚነሱ ዋና ዋና ጥያቄዎች<br>• ህዝቡ በኢትዮጵያ ላይ ያለው አመለካከት<br>• መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር ያለው ግንኙነት፣ በተጨባጭ የተደረገ ድጋፍ<br>• Multilateral ግንኙነት ካለ ምን ይመስላል?<br>• በሀገሪቱ ያሉ ዋና ዋና የትምህርት ተቋማት፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ትላልቅ ካምፓኒዎች፣ የግብረ ሰናይ ድርጅቶች ወዘተ ምን ይመስላሉ? | • በሚሲዮኑ ፖሉቲካና ፐብሊክ ዲፕሎማሲ<br>• ከአስፈላጊ ግለሰቦች<br>• ከኢንተርኔት | | |
| 4.2 | ስለዲያስፖራው ሁኔታ | | | |
| 4.2.1 | የኢትዮጵያ ዲያስፖራና/ትግራይ ተወላጅ እንዴት እንደመጡ<br>• ከአፄው ስርዓት፣ በደርግ፣ በኢህአዴግ እንዴት እንደነበረ፣ መነሻው ምን እንደሆን<br>• በየትኛው ከተማ ነው የሰፈረው?<br>• ማን የት እንዳለ ይታወቃል? የተደረገ ጥረት ካለ | | | |
| 4.2.2 | ዲያስፖራው በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበረው ሁኔታ<br>- በደርግ፣ በአፄ ኃይለ ስላሴ፣ በኢህአዴግ በመደገፍ ወይም በመቃወም የነበረው አደረጃጀት፣ እንቅስቃሴ፣ ዋና ተዋናዮች ምን ይመስሉ ነበር?<br>- የህወሐት አባላት በትግሉ ወቅት<br>• አደረጃጀቱ ምን ይመስል ነበር? | • የህወሐት መሰረታዊ ድርጅት አባላት<br>• በትግሉ ሲንቀሳቀሱ ከነበሩ ግለሰቦች | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • ያደረጉት ተጨባጭ አስተዋፅኦ ምን ይመስል ነበር?<br>• የነበሩ ዋና ዋና ተዋናዮች እነማን ነበሩ?<br>• የዚህ ትግል አስተዋፅኦ እንዴት ይታወሳል፣ ለአሁኑ ትውልድ እንዴት ተላልፈዋል? | | |
| 4.2.3 | ዲያስፖራው በሀገሪቱ (UK) የሚደርስበት ችግሮች<br>• በተደጋጋሚ የሚያነሳቸው ችግሮች ምን ምን ናቸው?<br>• የሀገሪቱ መንግስት፣ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ያደረጋቸው መፍትሄዎች ምን ምን ናቸው?<br>• የተለየ ችግር የሚደርስባቸው (social group) ካሉ | • ከልማት ድርጅቶች<br>• ከሚሲዮን (ዲያስፖራ)<br>• ከተለየዩ ግለሰቦች | |
| 4.2.2 | ዲያስፖራ ከአገራችን ጋር በተያያዘ የሚያነሳው ጥያቄ<br>• በአጠቃላይ የልማት የሰላም ዲሞክራሲ ሂደት ላይ የሚያነሳቸው ቅሬታዎች (በአገር - ክልል)<br>• ከራሱ ጋር በተያያዘ የሚያነሳቸው ሁኔታዎች<br>• ኤምባሲው በሚሰጠው አገልግሎት የሚያነሳቸው ቅሬታዎች | • ከኤምባሲው ቪዛ አገልግሎት<br>• ከማህበራት<br>• ከሌሎች በግል | |
| 4.2.4 | ከዲያስፖራው የተለያዩ ድርጅቶች<br>• የልማት፣ የኮሚኒቲ ወይም ሌሎች ...<br>• የአባላቱ ብዛት፣ ዓላማቸው ምንድነው፣ የዕ/ቤታቸው አጠቃላይ አድራሻ፣ የስብሰባ ግዜ ሀግና ደምብ ወዘተ...<br>• የአመራሩ ማንነትና ተቀባይነት እንዴት እንደሆነ፤<br>• የግንኙነታቸው መንገድና ሁኔታ ምን ይመስላል?<br>• ለተቋቋመበት ዓላማ ያበረከቱት አስተዋፅኦ በገንዘብ፣ በፕሮጀክት፣ በሙያ ወዘተ ምን ይመስላል (በዝርዝር)<br>• ከመንግስት ጋር ያላቸው ግንኙነትና ...<br>• አባላቱና አመራሩ ያላቸው ግንኙነትና የሚነሱ ጥያቄዎች ካሉ?<br>• በቀጣይ የወጣቶች፣ ሴቶችና ነጋር ታጋዮች የሙያ ወዘተ በተለያየ ፍላጉት ለማደራጀት በሚሲዮኑ የተደረገ እቅድ፣ ተግባር ውጤት<br>• በድርጅቶች መካከል ... ምን እየተደረገ ነው?<br>• ለሚያደርጉት አስተዋፅኦ የምስጋና ፕሮግራም የተዘጋጀ ካለ?<br>• በህዝብ ስም ተራጅተው በተቃዋሚ ፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚሳተፉ ካሉ? | • የTDA አመራር አሁን ያሉትና የቀድሞ<br>• የTDA አባላት<br>• ከሚሲዮን (ዲያስፖራ የስራ ሂደት) | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4.2.6 | ዲያስፖራው ከአገሩ ባህል ጋር ለማዛመድ (አዲሱን ትውልድ) ያለው ሁኔታ<br>• ይህን የሚመለከት አደረጃጀት ካለ ( )<br>• የሃይማኖት ተቋማት ካሉ (እንደ ቤተክርስቲያን) የሚሰሩት ስራ<br>• ከባህል ኪነት፣ የቋንቋ፣ የፊደል ትምህርት፣ የጉብኝት ወዘተ ስራ የሚተሳሰር የlong term ስራ ካለ<br>• የወጣቱ ዝንባሌ፣ ከአገሩ ጋር ለመስራት ያለው ፍላጎት፣ እንዴት መገኘት ይቻላል? | • ከድርጅት TDAሌላ ማህበር ካለ<br>• ከዲያስፖራ (ሚሲዮን)<br>• ከተለያዩ ክለቦች<br>• ከተለያዩ ወጣቶች ጋር | | |
| 4.2.7 | ዲያስፖራው ከቢዝነስ፣ ከልማት ከመሳሰሉት ስራዎች ጋር ያለው ትስስር በሚመለከት<br>• በተለያዩ የቢዝነስ፣ ንግድ ስራዎች የተካፈሉ ይታወቃሉ (በግል፣ ማህበር፣ Joint Venture)<br>• በJoint Venture ይሁን በግል invest ለማድረግ ያለ አቅም ምን ይመስላል?<br>• ቤት ልማት ማህበር ተደራጅተው የተሳተፉ ማህበራትና አባላት ይታወቃሉ?<br>• በዚህ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በፖሊሲ፣ አሰራር፣ አፈፃፀም የሚያነሱት ጥያቄ<br>• የተደረጉ ኢንቨስትመንቶች የመንግስት መረጃ በመጠቀም ነው ከfree market ጋር በመሄድ ነው?<br>• በአገራችን ያሉት አማራጮች ግልፅ ናቸው?<br>• የቢዝነስ network እንዴት ሞኒተር ይሆናል (ከአገር ጋር)<br>• የውጭ ባለሀብቶች ከአገራችን በimport በማድረግ ይሁን በFDI ይሳተፋሉ (በቁጥር) ... ከሀገራችን ባለሀብቶች ጋር፣ እዚህ ካለው ዲያስፖራ ጋር jointly ለመስራት ያለው ሁኔታ፣ የሚያነሱት ጥያቄዎች ምን ይመስላል? | • ከሚሲዮን ቢዝነስና ኢኮኖሚ<br>• ከሚሲዮን ዲያስፖራ<br>• ከተለያዩ የልማት ማህበራት<br>• ከግለሰቦች<br>• የባንክ ሙያ ካላቸው ሰዎች | | |



| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | • ወደ አገር ቤት ሄደው አዲስ ነገር ይጨምራሉ የሚባሉ፤ በአመለካከት ደረጃ ቀና አስተሳሰብ ያላቸው እነማን ናቸው? ከየት ዩኒቨርሲቲ ይገኛሉ?<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግር በተመለከተ<br>- በሀገራችን በዚህ ጉዳይ ከUK የሚፈለገው ነገር ግልፅ ሆኗል? ምን<br>- የጥናት ተቋማት (research) ተለይተዋል (ከኛ ጋር የሚሄዱ) እነማን?<br>- ለዲያስፖራው በትምህርት፣ ጤና .. ወዘተ እዚህ የተደራጁና ፍላጎት ያላቸው ካሉ? የተሰራ ስራ ካለ? | | | |
| 4.2.8 | የዳያስፖራው remittance አካውንት መክፈት<br>• የ remittance እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?<br>• ህጋዊ መልክና ህጋዊ ባልሆነ መልክ እንዴት ይሉካል (ያለው ችግር)<br>• የሀገራችን ባንኮች ... ምን ይመስላል? የተደረገ መፍትሄ ካለ?<br>• በሀገራችን ስም ባንክ አካውንት ያከፈቱ ስንት ናቸው? የሚነሳ ችግር፤ በቀጣይ ያለው trend ምን ይመስላል? | • ከዲያስፖራ (ሚሲዮን)<br>• ከልማት ማህበራት<br>• ከግለሰቦች<br>• ከባንክ ባለሙያዎች | | |
| 4.2.9 | ዲያስፖራውና የቦንድ ሽያጭ<br>• እስካሁን በገንዘብ የተሰበሰበው (ስንት፤ መቼ፤ ከማን)<br>• ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የተቋቋመው አደረጃጀት (ምን ይመስላል፤ ጠንካራና ደካማ ጎኑ)<br>• ቦንድ የገዙት ሰዎች ምን ይመስላሉ ... አጠቃላይ አመለካከታቸው ወዘተ ከነሱ ጋር በቀጣይ ለመስራት የተሰራ ስራ ወይ የታሰበ ነገር ካለ?<br>• ቦንድ በሚመለስት በአሰራሩ፤ በአስፈላጊነቱ የሚነሱ ጉዳዮች ካሉ | • ከልማት ማህበር አመራር ጋር<br>• ቦንድ ከገዙ ደጋፊና neutral ሰዎች ጋር<br>• ከዲያስፖራ (ሚሲዮን ጋር) | | |
| 4.2.10 | ብሄራዊ መግባባት ላይ እየተሰራ ያለ ስራ<br>• በአመራሩ የዚህ ጉዳይ ምንነት ግልፅ መግባባት ካለ? ምን ትርጉም ይሰጡዋል?<br>• ቦንድ ከገዙትና ከሌላ ተሳትፎ ካላቸው ጋር እየተካሄደ ያለው ስራ | • ሚሲዮን (ዳያስፖራ)<br>• የልማት ማህበራት<br>• የቦንድ ምክር ቤት የተወሰኑ አባላት | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ምንድን ነው?<br>• አንድ ለ5 የሚባለው አደረጃጀት ተጀምሯል? በዚህ ላይ ያለው ተመክሮ ምንድን ነው? እንዴት ይገባል? | • ከመሰረታዊ ድርጅቶች<br>• ከሌሎች neutral ሰዎች ጋር | | |
| 4.2.11 | ዲያስፖራውና የመረጃ (information) ስራ<br>• ዲያስፖራውን መረጃ ለመስጠት ምን እንጠቀማለን?<br>• ዲያስፖራው የሚፈልገው ግንኙነት መንገድ (ስብሰባ፣ ጋዜጣ፣ ሚዲያ፣ ኢንተርኔት፣ ኢቴቪ ወዘተ የትኛውን ይፈልጋል?) ለምን?<br>• በሚዲያ በኩል በተለያየ መንገድ እየሰሩ ያሉ (ዕሁፍ፣ ሬዲዮ፣ ... ደጋፊዎች ተቃዋሚ እነማን ናቸው ያላቸው ሁኔታ<br>• ዲያስፖራው በየክልሉ ያለው የመረጃ ልውውጥ ምን ይመስላል?<br>• ወሬውን የሚያገቡ ዋና ዋና መሳሪያዎች፣ ሆቴሎች ሌሎች መገናኛ ቦታዎች፣ አደረጃጀቶች እነማን ናቸው?<br>• አገር ቤት የሚሄዱ ሲሄዱና ሲመለሱ ምን ይደረጋል?<br>• ዲያስፖራው የሚገኝበት የባህል ምግብ ቤት፣ ሱቅ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የተለያዩ መድረኮች ይታወቃሉ? እነዚህን ለመጠቀም የተደረገ ነገር ካለ፣ ከሌለ ለወደፊቱ እንዴት ይቻላል?<br>• ተሰሚነት ያላቸው ግለሰቦች ተለይተዋል? እነማን ናቸው? እነዚህን ለመጠቀም ምን ተሰርቷል? ለወደፊቱስ ምን መስራት ይቻላል?<br>• ተሰሚነት ያላቸው የኪነት ሰዎች አሉ? እንዴት እንጠቀምባቸዋለን?<br>• ዲያስፖራን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደምቦች፣ መመሪያዎች ይታወቃሉ? ለቀጣይ ምን መስራት አለበት? | • ከልማት ማህበር<br>• ከዲያስፖራ ሚሲዮን<br>• ከተለያዩ neutral የሆኑ ሰዎች | | |
| 4.2.12 | ሌሎች ስለዲያስፖራው መጠቀስ ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ | • | | |
| 4.2.13 | ስለኢህአዴግ ድርጅቶች<br>• አደረጃጀቶች ካሉ እንዴት በብዛር፣ በኢህአዴግ ደረጃ ተደራጅተዋል? በዚህ አገርና አገር ቤት ያላቸው የአደረጃጀት ግንኙነት ምን ይመስላል?<br>• ስንት አባላት አሉ? | • | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | • በምልመላ የሚያጋጥም ችግር (በብዛት፣ በዓይነት፣ በፍላጐት) ለወደፊቱ ምን ቢደረግ የተሻለ ይሆናል?<br>• የድርጅት አባላቱ ለሌላው አብነት በመሆን (influence በማድረግ) ያላቸው ሚና<br>• የአባላቱ የመዋጮ፣ የስብሰባ (ውይይት)፣ የስራ ግምገማ፣ ወዘተ ስርዓት ምን ይመስላል?<br>• በአጠቃላይ በዚህ በኩል ያለው ተጨባጭ ችግሮችና መፍትሄዎች ምን ቢሆኑ ይሻላል? | | | |
| 4.4 | የተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚመለከት<br>• ዋና ዋና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ማን ይባላሉ?<br>• አመራሩ (ዋና ዋና) ማን ይባላሉ?<br>• የሚንቀሳቀሱበት ሃሳብ ምንድን ነው?<br>• የአባላቱ ብዛትና፣ ያላቸው ድጋፍ ይሁን በአባላቸው ሳይቀር የሚነሱ ተቃውሞዎች ምንድን ናቸው?<br>• የሀገሩን መንግስት influence በማድረግ ደረጃ ያላቸው ሚና<br>• ሰዎችን ለማግኘት፣ ለማደናገር የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ምንድን ናቸው?<br>• ... አሰራራቸው ምን ይመስላል<br>• በተቃውሞ በዋናንት የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች እነማን ናቸው? ስም | • ከመሰረታዊ ድርጅት ጋር<br>• ከልማት ማህበር<br>• ከሌላ ከሚመለከታቸው ጋር | | |
| 4.5 | የኤርትራ ማህበረሰብ<br>• ያለው የዲያስፖራ ብዛት (የሚንቀሳቀሱበት አካባቢ የት ነው)<br>• ያላቸው አደረጃጀት (የመንግስት ደጋፊዎች ተቃዋሚዎች)<br>• ከሀገራችን ጋር ያላቸው አመለካከት ከኛ ጋር ተባብሮ ለመስራት ያለ ፍላጐት | | | |
| 4.6 | የኤምባሲው አሰራር (ሚሲዮን)<br>የስብሰባ፣ የስራ ግምገማ ወዘተ ግንኙነቶች ምን ይመስላሉ?<br>አጠቃላይ ያለው የስራ ግንኙነትና በዲያስፖራ ስራ ላይ ተባብሮ ለመስራት ያለው ሁኔታ<br>የሚነሱ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች | | | |